# ሰዉን እንዲህ ምን አደደበው?

ሰሞኑን በተለምዶ ቆሸ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተፈጸመው አደጋ ለተጎዱ ወገኖች አንዳንድ አካላት ድጋፍ እርዳታ እየለገሱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በማኅበራዊው የብዙኃን መገናኛ ለተጎጂ ወገኖች ከሁለት አቅጣጫ ማለትም ከአዲስ አበባ መስተደደር እና ከሼክ ሙሐመድ አሊ አልአሙዲን ለመጡ ድጋፍና እርዳታዎች የሞቀ ምስጋና እና አድናቆት ሲጎርፍ ስመለከት በጣም ግራ ተጋባሁና "ይሄንን ሕዝብ እንዲህ አድርጎ ምን አደደበው?" እንድል አደረገኝ፡፡ ደሞ በጣም የገረመኝ ነገር ከእነኚህ አድናቂ አመስጋኞች ውስጥ በተቃውሞ የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ጎራ ውስጥ ነን፣ አክቲቪስት (ስሉጥ) ነን፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ነን፣ ጋዜጠኛ ነን… የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖችም መገኘታቸው ነው፡፡ በጣም አይገርምም? እነኝህ ሰዎች ደመነፍሳቸውን ነው እንዴ ለካ የሚንቀሳቀሱት? ለካ ምን እየተካሔደ እንዳለ ምንም የሚያውቁት እና ምን እየተካሔደ እንዳለ የማወቅ የመረዳት አቅም፣ ብቃት፣ ንቃት የሌላቸው ገልቱና ገለባዎች ናቸው ለካ!

ወያኔ ዜጎችን ካሉበት ከሠፈሩበት ቦታ አጽድቶ ቦታውን ለባዕዳንና ለናጠጡ ባለሃብቶች ለመቸብቸብ ሲፈልግ ምን ሲያደርግ እንደኖረ ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ እሳት ይለቅና አካባቢውን በፀጥታ ኃይል አስከብቦ ያሳጥራል፣ ማንም ገብቶ ንብረቱን ማውጣት ማትረፍ እንዳይችል በፀጥታ አካላቱ ይከለከላል፣ የእሳት አደጋ መከላከያ ኃይል ይገባል የሚረጨው ውኃ ግን እሳቱን ለማጥፋት የሚረዳ ሳይሆን የሚያባብስ ኬሚካል (ንጥረ ቁስ) የተጨመረበት ውኃ ነው፡፡ ለዚያም ነው እንዲቃጠሉ የተደረጉ አካባቢዎችና መደብሮች እሳት አደጋ ገብቶ እያለ ሊተርፉ ሲገባ አንድ ነገር ማዳን ሳይችል እንዳለ አመድ የሚሆኑበት ምክንያት፡፡

አሁን ደግሞ በቆሸ እንደታየው ለወሬ ነጋሪ አንድ ሰው እንዳይተርፍ አድርጎ በደማሚት የማደባየት አዲስ ዘዴ ተይዟል፡፡ የቆሸ አደጋ ከመከሰቱ በፊት የተስተዋሉ ነገሮች በሙሉ ይሔንን የሚያረጋግጡ ሆነዋል፡፡ አደጋው ከመከሰቱ በፊት የአዲስ አበባ መሥተዳድር ለነዋሪዎቹ ቦታው ለልማት ስለሚፈለግ ነዋሪዎችን እንዲለቁ አሳስቦ ስለነበረ ነዋሪዎቹ ለመልቀቅ ፈቃደኞች መሆናቸውን ተናግረው ነገር ግን ምትክ ቦታና ለሚፈርሰው ቤታቸው ካሳ ቢጠይቁም መሥተዳደሩ ይሄንን እንደማያደርግና በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ ያስጠነቀቀ መሆኑ፣ አደጋው ሊከሰት አንድና ሁለት ቀናት ሲቀሩት ቦታው በፀጥታ አካላት መከበቡ፣ የአደጋው ዕለት ማታ ደማሚት እየተዘረጋ እንደሆነ በተጠረጠሩ የመንደሩ ክፍሎች ሰው እንዳይዘዋወር መከልከሉ፣ አደጋው በተከሰተበት ቅጽበት ፍንዳታ መሰማቱ፡፡ እነኝህ ነገሮች ቁልጭ አድርገው የሚያረጋግጡት እውነት ቢኖር አደጋው እንዲደርስ የተደረገው ሆን ተብሎ መሆኑን ነው፡፡

እና ታዲያ ደናቁርት ሆይ! ይሄንን ሁሉ መዓት በወገኖቻችን ላይ ያወረደው የአዲስአበባ መስተዳድር (ወያኔ) ለተጎጂ ቤተሰቦች እንዲህ እንዲህ አደረገ ተብሎ ሊመሰገን የሚገባው በምን ሒሳብ ነው?

በመኖሪያ መሬታችን እንዲህና እንዲህ በመሳሰለ ግፍ እንድንወገድ ተደርጎላቸው ወይም አስደርገው መሬታችን የሚሰጣቸው ሼህ አላሙዲንና መሰል ባለሀብቶች ለተጎጂ ቤተሰቦች እንዲህ እንዲህ አደረጉ ተብሎ እንዴት ነው ሊመሰገኑ ሊደነቁ ሊከበሩ የሚገባው???

ጭራሽ ማሰቢያቹህ ተደፍኖ ቁጭ አለ? በዚህ ሁኔታ ይሄ ሕዝብ የፈለገ ነገር ቢደረግበት ግፍ በቃኝ! አሻፈረኝ! ብሎ ራሱን የመታደጉ ነገር ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር መሆኑ ነው ማለት ነው፡፡ ታዲያ ይሄ ሕዝብ እንዲህ መጫወቻ

ለመሆን ከፈቀደ እኔ ምን አቃጠለኝ? ምን አስጨሰኝ? ሲፈልግ ለምን አራት እግርህን ነቅሎ ቀቅሎ አይበላህም! ድራሽህን ያጥፋው!!!

እነ አላሙዲንና መሰል ባለሀብቶች ሆይ! እውነት የምታስቡልንና የምታዝኑልን ከሆነ እንዲህ ባለ ኢሰብአዊ ግፍ ከያለንበት ቦታ እንድንፀዳ፣ እንድንወገድና መሬቱ እንዲሰጣቸው አታድርጉ፡፡ በዚህ መልኩ ሕዝብ በገዛ ሀገሩ ተረጋግቶ የመኖር ሰብአዊና የዜግነት መብቱ ተገፎ በግፍ እንዲወገድ ተደርጎ የሚሰጣቹህን የደም መሬት አንቀበልም! አንፈልግም! በማለት የሚፈጸምብን ግፍ እንዲቆም ተባበሩን፡፡ ካልሆነ ግን ይህ ድርጊታቹህ የሚያሳየን ሽፍጠኝነታቹህን ነውና፣ በሕይዎታችን ቁማር እየተጫወታቹህብን መሆኑን ነውና የአዞ እንባቹህን እያነባቹህ ለምትሳለቁብን ተሳልቆ ዋጋቹህን ከእኛም ባይሆን ግፍን ከሚቆጥረው አምላክ ጠብቋት ታገኟታላቹህ!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

*http://www.ethiopanorama.com*